27/02/2010ዓ/ም

# መሪ ማነው?ማንኛውም የተማረው ወይስ መድረክ የፈጠረው?

# የወቅቱ ጥያቄ በኢትዮጵያ

በአገራችን የተከሰተው ግዝያዊ አለመረጋጋት ተከትሎ ያገበኛል የሚል ኢትዮጵያዊ ዜጋ መፍትሄ የሚለውን አስተያየት እያቀረበ ይገኛል፡፡ይህን ገንቢ በሆነ መንገድ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል በብዙዎች ዘንድ ይታመናል፡፡ኢህአዴግ በበኩሉ መፍትሄ የሚለውን እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡እየተወሰዱ ካሉት እርምጃዎች ውስጥ ጥልቅ ተሃድሶ ማካየድ፣ከከፍታኛ ኣመራር እስከ መካከለኛ ኣመራር ስልጠና መስጠት፣የኢህአዴግ ኣባል ድርጅቶችና ኢህአዴግ በቅርቡ ድርጅታዊ ጉባኤ ለማካየድ መዘጋጀትን ያጠቃልላል፡፡የዚህ ፅሑፍ ኣላማም ኢህአዲግ እየወስዳቸው ያለ እርምጃዎች ላይ ኣስተያየት ለመስጠት ነው፡፡

ኢህአዲግ ኣሃዳዊ ስርኣት ከስርመሰረቱ ነቅሎ በመጣል በምትኩ ብዝሃነትን የሚያስተናግድ ዲሞክራስያዊ ስርኣት በኢትዮጵያ ለመገንባት የተራዘመ የትጥቅ ትግል ያካየደ ድርጅት ነው፡፡በተራዘመ የትጥቅ ትግል ጉዞ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች በማንቃት በማደራጀትና በማስታጠቅ ደርግን ለመጣል ቻለ፡፡

ኢህአዲግ ደርግ ከደመሰሰ ብኋላ ስልጣን ብቻየን ልያዘው ኣላለም፡፡ነፍጥ ኣንግበው በረሃ ከነበሩት ግን ያልተሳካላቸው እንዲሁም ኣዳዲስ ከተመሰረቱት ድርጅቶችም የሽግግር መንግስት ለማቋቋም ተንቀሳቀሰ፡፡ይህም ተሳክቶለት ሽግግሩ መንግስት ተመሰረተ፡፡ይህ የሽግግር መንግስት ኣገር የማረጋጋት ህገ መንግስት እንዲረቅና ህዝብ በወከላቸው ተወካዮች እንዲፀድቅ የማድረግ ተልእኮውን ይዞ ተንቀሳቀሰ፡፡የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፓብሊክ ህገ መንግስት በብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች ተወካዮች ፀደቀ፡፡ኣሃዳዊ ስርዓት ላንዴና ለመጨረሻ በዚህ ህገ መንግስት ፈረሰ፡፡በምትኩ ፌደራላዊ ስርኣት ታወጀ፡፡

ይህ ፌዴራላዊ ስርዓት የትብብር ስርኣት ነው፡፡ክልሎች ራሳቸውን ችለው የሚያስተዳድሩበት ኣከባብያቸውን የሚያለሙበት በንቁ የህዝብ ተሳትፎ መልካም ኣስተዳደር የሚሰፍንበት ልማት የሚፋጠንበት ህዝቡ ከልማቱ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ስርዓት ነው፡፡የግልም የቡድንም መብት የሚከበርበት ነው፡፡ብሄሮች ብሄረ ሰቦች እስከ መገንጠል መብታቸው የሚከበርበት የሴቶች የሃይማኖቶች እኩልነት የሚረጋገጥበት ነው፡፡በኢትዮጵያ እሆነ ያለውም ይኸው ነው፡፡ልማት ተፋጥነዋል የግልና የብዱን መብት፣የብሄር ብሄረሰብ ባህላቸው ቋንቋቸው ተከብራዋል ክልላቸው በራሳቸው እያስተዳደሩ ማልማት ችለዋል፡፡የመድብለ ፓርቲ ስርዓትም በኢትዮጵያ እውን ህኖዋል፡፡

በማጠቃለል ኢህአዲግ በኢትዮጵያ ለመጣው ኣጠቃላይ ኣመርቂ እድገት በብቃት መርተዋል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢህአዲግ ኢትዮጵያን በሚመራበት ግዜ ምንም እንከን

አለጋጠመውም የሚባል አይደለም፡፡1983ዓ/ም ደርግን ከደመሰሰ በኋላ ፈታኝ ሁኔታ የጋጠመው በ1993ዓ/ም የተሃድሶ እንቅስቃሴ ነው፡፡ድሪቶውን አመለካከት አስወግዶ አዲሱ የጠራ መስመር ከመከተል አንፃር በድርጅቱና በህዝቡ ውስጥ ሰፊ እንቅስቃሴ ተካሂደ፡፡ምለአተ ህዝቡ የተሳተፈበት ስለነበር የህዳሰው ሃይል አሸንፎ ወጣ፡፡ከዚህ ግዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፈጣን የሚባለው ፖለቲካዊ ኢኮኖምያዊ እድገት ተመዘገበ፡፡በሰላም ማስከበር፣በህዳሴ ግድብ ፣ በአረንጋዴ ልማት ወዘተ በዓለም ከፍተኛ ተደማጭነት እያገኘች ያለች ሃገር እስከመባል ደረሰች፡፡በዓለም ደረጀ ለተገኘው ተደማጭነትም ኢህአዴግ በብቃት በመምራቱ የተገኘ ነው፡፡

አንባብያን በኢትዮጵያ እዛም እዚህም የሚታይ ያለ አለመረጋጋት ታድያ ከምን የመነጨ ነው?በማለት መጠየቃቸው አይቀርም፡፡የተላያዩ ወገኖች ለዚህኛው ጥያቄ የተለያየ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡አንዱ ወሳኙ ምንጭ ከኢህአዴግ ውጭ ባሉት ሃይላት የሚፈጠር አድርጎ ማቅረብ ይችል ይሆናል፡፡አንዱ ደግሞ ወሳኙ የችግሩ መንስኤ በኢህአዴግ የሚስተዋሉ ችግሮች አድርጎ ሊያቀርቦው ይችላል፡፡ወሳኙ ችግር ለይቶ ማወቅ መሰራታዊ መፍትሄም ለማስቀመጥ ስለሚያግዝ በጥልቀት ማስተዋልን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ቀጥለን በዝርዝር ወድምናይበት ጉዳይ እንሸጋገር፡፡

በቅድምያ ከኢህአዴግ ውጭ ያሉትን ሁኔታዎች እንመልከት፡፡አሁን ለተፈጠረው ሁኔታ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሰው የሊበራሉ ሓይል ነው፡፡

የሊበራል አለም በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አሰተሳሰብ ላይ ሰፊ ጥቃት እየሰነዘረ እንዳለ ይታወቃል፡፡አብዮታዊ ዲሞክራሲ በመሬት፣በህዝብ ስልጣንና ተጠቃሚነት፣የራስህን እድል በራስህን የመወሰን እስከ መገንጠል ከኢትዮጵያ የተለየ ባህሪ በመነሳት የወሰዳቸውን አቋሞች የሊበራሉ ጥቃት ዒላማ መሆናቸው ይታወቃል፡፡የሊባራል ሃይሎች ጥቃት እየፈፀሙት ያሉት በሁለት መንገድ ነው፡፡አንዱ መንግድ የውጭ መንግስታት በቀጥታ የኢትዮጵያን መንግስት ጫና በመፍጠር ያለውን አቋም እንዲቀይር አልያም እንዲያለዝብ ማድረግ ነው፡፡ይህንን አካየድ ሳያዛልቃቸው ቀርተዋል፡፡ብቅ ጥልቅ የሚለው ባአብዛኛው ኢትዮጵያ በድርቅ ስተመታ ነበር፡፡ይህም በራስዋ አቅም ድርቅ መመከት ስትጀምር ረገብ ማለት ጀመረ፡፡ይህ ሁኔታ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ ሊፈጥር የሚችል አለመራጋጋት ሊወስን እንደማይችል ነው፡፡የውስጣችን አቅም በተጣነከረ ቁጥር ሊፈጥሩት የሚችሉትን ጫና ይበልጥኑም እየቀነሰ የሚሄድ ነው፡፡

ሁለተኛው መንገዳቸው የቀለም አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ተላላኪዎቻቸው አማካኝነት በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ መመከር ነው፡፡ይህ አሁንም እተገበሩት ነው፡፡ይህንን ሂደት በኢትዮጵያ አለመራጋጋት እንዲኖር የማድረግ አቅሙ በቀላሉ ሊገመት አይገባውም፡፡ይህም ኢህአዴግ ጠንክሮ በመስራት የሚፈጥሩት ሴራ ክህዝቡ ጋር በመተባበር ሊያከሽፈው የሚችል ስለሆነ ለተፈጠረ ችግር ወሳኝነት ነበረው የሚባል አይደለም፡፡

ሌላ እንደምክንያት የሚጠቀሰው የግብፅና የኤርትራ ገዢ መደቦች እየሸርቡት ያሉትን ሴራ ነው፡፡የግብፅ ገዢ መደቦች በግብፅ ስልጣን ይዘው ለመቀጠል የሚይስችላቸው ዋነኛ መንገድ ህዝብን ተጠቃሚ የሚደርግ የጠራ መስመር በመከተል አይደለም፡፡በግብፅ ምድር በቅርብ ርቀት የሚሆን አይደለም፡፡አሁን በግብፅ ምድር ወደስልጣን መውጣትና በስልጣን መኖር የሚቻለው በአባይ ዙርያ የሚነሱ ጉዳዮች በተጣመመ መንገድ በማቅረብ ይህም አሚጥጦ በመጠቀም የግብፅን ህዝብ ሓቀኛ ጥቅሙን እንዳያይ አይኑን በመጨፈን ነው፡፡በዚህ ምክንያት የግብፅ ገዢ መደቦች በኢትዮጵያ ላይ ሴራ ማሴራቸው አያቆሙም፡፡በኢትዮጵያ ላይ የሚታየው ያለው ይህንኑ ነው፡፡ይህ ጉዳይም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ተላላኪዎች የሚፈፀም ስለ ሆነ ይህም ወሳኝ ምክንያት ነው ሊባል አይችልም፡፡

ከውጭ ሃገራት ገዢ መደቦች ሊሰነዘር ከሚችል ጥቃት አንዱ ከዳካማው የኤርትራ መንግስት ሊሰነዘር የሚችል ጥቃት ነው፡፡የኤርትራ ገዢ መደብ በስልጣን ለመቆየት ሲል የኤርትራን ነፃነት በኤርትራ ህዝብ የተገኘ መሆኑን ቀርቶ ህግደፍ/ሻዕብያ/ብቻው ባደረገው ትግል ብቻ የተገኘ አድርጎ በማቅረብ በኤርትራ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለመኖር ጥረት እያደረገ ነው፡፡ሻዕብያ በሰጠው መሪነት ኤርትራን የተራጋጋች አገር ሌሎቹ ደግሞ መረጋጋት ያቃታቸው ሃገር ለማስመስል ቀጠናው የመተራመስ ዕቅድ በመንደፍ እየሳራ ነው፡፡አሁን የሚታየው ያለው ግዝያዊ አለመራጋት የሻእብያ እጅ እንዳለብት በግልፅ እየታየ ነው፡፡

የግብፅና የኤርትራ ገዢ መደቦች የሚያሴሩት ሴራ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ተላላኪወች የሚከወን ስለሆነ ተላላኪዎቹ በሚከስሙበት ግዜ ኣብሮ የሚከስም ስለሆነ ይህም ወሳኝ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጥሩት የሚችሉት ችግር በማንኛውም መመዘኛ ኣሳንሶ ማየት የሚጠቅም አይደለም፡፡ተገቢውን ግምት ሰጥቶ መታገልና ሴራቸውን ማክሸፍ ይጠይቃል፡፡ወሳኙ ሴራቸው ማክሸፍያ መንገድም በኢትዮጵያ ጠንካራ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ያለው ኣንድ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ የኢትዮጵያ የውስጥ ሁኔታዋ ሲታይ በሁለት ወሳኝ ፖለቲካዊ ኣሰላለፍ የተከፋፈለች ሃገር ናት፡፡ኣንዳኛው ፖለቲካዊ ኣሰላለፍ የክራይ ሰብሳቢዎች ኣሰላለፍ ነው፡፡ሁለታኛው ደግሞ የልማታዊ ዲሞክራሰያዊ ሓይሎች ኣሰላለፍ ነው፡፡

በክራይ ሰብሳቢዎች ፖለቲካዊ ኣሰላለፍ ሊታዩ የሚችሉት የመንግስትን ስልጣን ተጠቀመው እሴት ሳይጨምሩ ለመክበር የሚፈልጉትን ሃይሎች ይገልፃል፡፡እነዚህ ሃይሎች ትምክህትም ጠባብነትም ሃይማነትን በሽፋንነት የሚጠቀሙ ናቸው፡፡እነዚህ ሃይሎች በስልጣን እርከንም የተቀመጡ፣ከስልጣን ውጪ ሁኖው ፖለቲካዊ ድርጅት የፈጠሩ ኣልያም የፖለቲካዊ ድርጅት ሳይኖራቸው እንደዜጋ በኣገር ውስጥም በውጪ ኣገር የሚኖሩ ያካትታል፡፡የነዚህ የክራይ ሰብሳቢዎች ፖለቲካ ኣቀንቃኞች ሁኖው ብዙን ግዜ የምናያቸው የደርግ፣የኢህኣፓ፣መኢሶን፣ኢዲህ፣ኦነግ ቅሪቶች ወይም የነዚህ ክራይ ሰብሳቢ ሃይሎች

መንፈሱ የሰረፃቸው ሁኖው እናገኛቸዋለን፡፡እነዚህ ሰዎች የድሮ ታሪካቸው በመሸፈን ኣዲስ ፓርቲ በመመስረት የዲያስፖራ ታርጋ በመለጠፍ የክራይ ሰብሳቢ ፖለቲካቸው ያከናውናሉ፡፡ከነዚህ ወገኖች ስብስብ ውስጥ ኣዲሱ ትውልድ ኣልተቀላቀባቸውም የሚባል ኣይደለም፡፡ይህ ኣዲሱ ትውልድ ወደነዚህ የተቃለቀለው በተለያየ ምክንያት ቢሆንም በዋነኝነት ትክከለኛ ጥቅሙን ባለ መገንዘብ ነው፡፡እነዚህ የክራይ ሰብሳቢ ሃይሎች ዋና ኣላመቸው ለክራይ ሰብሳቢ ፖለቲካል ኢኮኖሚ የተመቸ ሁኔታን በኢትዮጵያ እንዲፈጠር ነው፡፡ይህ ኣመራጭ በኢትዮጵያ ትርምስን ሊያስከትል ካልሆነ በስተቀር መረጋጋትን ሊፈጥር ኣይችልም፡፡ይህ የክራይ ሰብሳቢዎች ኣሰላለፍ ትርምስን የሚፈጥር ነው የሚባልበት ምክንያት ከሁለት በላይ የተከፋፈለ ሃይል በመሆኑ ነው፡፡ኣንዳኛው የክራይ ሰብሳቢዎች ፖለቲካዊ ኣሰላለፍ ትምክህተኛው ሓይል ነው፡፡ይህ ሓይል ፌዴራላዊ ስርኣት ፈርሶ ኣሃዳዊ ስርኣት በኢትዮጵያ እንዲያንሰራራ የሚታገል ሓይል ነው፡፡ሁለተኛ የክራይ ሰብሳቢዎች ኣሰላለፍ የጠባብ ብሄርተኝነት ሓይል ነው፡፡ይህም ሓይል ፌደራላዊ ስርኣት ፈርሶ የራሱን ጠባብ ግዛት የመፍጠር ዓላማ ያለው ነው፡፡ሰወስታኛው ሃይል ደግሞ የሃይማኖት ኣክራሪ ሃይል ነው፡፡ይህ ሃይል የሚከተለውን ሃይማኖት ብቻ እንዲቀጥል ሌሎች ሃይማኖቶች ከዚህ ምድር እንዲወገዱ የሚያደርግ ሃይል ነው፡፡ኣንድ መንግስት ኣንድ ሃይማኖት እንዲኖር የሚሰራ ሃይል ነው፡፡የራሱን ጠባብ ግዛት ለመመስረት የሚንቀሳቀስ፣በህዝቦች ትግል የተሸነፈው ኣሃዳዊ ስርኣት ተመልሶ እንዲመጣ የሚታገል፣በኢትዮጵያ ኣንድ ሃይማኖት ኣንድ መንግስት እንዲኖር የሚሰሩ ሃይሎች መቸውም ቢሆን ሊታረቁ ስለማይችሉ ነው የትርምስ ሓይሎች ናቸው የሚባለው፡፡በሌላ በኩል ኣንዱ እየበላ ኣንዱ ተመልካች የሚሆንበት ስርኣትም ከንግዲህ ሊፈጠር ስላማይችል ነው፡፡የክራይ ሰብሳቢዎች ፖለቲካ ሓይሎች ኣንዱ እየበላ ኣንዱ ተመለካች የሚሆንበት ስርኣት ለመፍጠር እየመኮሩ በመሆናቸው ነው የትርምስ ፖለቲካ ነው የሚባለው፡፡በኢትዮጵያ ኣሁን የሚሆነው ያለው ይህንኑ ነው፡፡እነዚህ የክራይ ሰብሳቢዎች ፖለቲካዊ ሃይል ስልጣን ላይ ባይቀመም ኣሁን ያለው ግዝያዊ ኣረመረጋጋት ተባብሶ እንዲቀጥል የማድረግ ኣቅሙ የሚናቅ ኣይደለም፡፡ይህ ሁከትና ብጥብጥ የማስቀጠል ዕድሉ ቀላል ኣይደለም፡፡ይህ ሓይልም ቢሆን የኢትዮጵያ እጣፈንታ የሚወስን ኣይደለም፡፡

ኣሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የኢትዮጵያ እጣፋንታ የሚወሱኑት የኢትዮጵያ ህዝቦችና የልማታዊ ዲሞክራስያዊ ሓይሎች ናቸው፡፡ኣሁን እየታየ ያለውን ግዝያዊ ኣረመረጋጋት ህዝቡ ጥቅሙን ለማስከበር የሚያደርገው ትግል መላላቱ ነው፡፡ብዙሃኑ ህዝብ እየደረሰበት የነበረ ብሄራዊ ጭቆና፣ከመሬቱ የመነቀል ችግር፣የፆታና የሃይማኖት ኣድልዎ በህገ መንግስታዊ ፌደራል ስርኣቱ ተሽንቀጥረው ሲጣሉ እፎይታን ተሰምቶታል፡፡ይህ ብቻ ኣይደለም ፈጣን ልማት በመምጣቱ ምክንያት ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል፡፡በዚህ ዘመን ይህን የመሰለ ለውጥ በኢትዮጵያ ሲመዘገብ የመጀመርያው ነው፡፡ይህንን የመሰለ ለውጥ ሊመዘገብ የቻለውም በኢህኣዲግ የመሪነት ዘመን ነው፡፡ሁሉንም ሓሳባቹና ችግሮቹ ለእዝጊሄር/ኣላህ/ እንደሚሰጥ ኣማኝ ብዙሃኑ ህዝብ ሙሉበሙሉ ሓሳቡ ለኢህኣዴግ በመጣሉ ምክንያት የተፈጠረ የትግል መቀዛቀዝ ነው፡፡ብዙሃኑ ኢህኣዲግን የተፈጠረው ያደገው እስከአሁን የነሮው ለወዲፍትም ጥቅሜን እያስጠበቀ ሊኖር የሚችለው በኔው በጋለ

ትግል ነው፡፡የኢህአዴግ ጌታ እኔ ነኝ ብሎ ትግሉ አጧጡፎ ካልቀጠለ አሁን እየታየ ያለው ግዝያዊ አለመረጋጋት ሊቀጥል ይችላል፡፡ስለዚህ ይህንን ችግር ለመፍታት የብዙሃኑ የጋለ ትግል መፍጠር ትኩረት መሰጠት አለበት፡፡

ኢህአዲግ ብዙሃኑ በኢትዮጵያ ምድር ጌታ ለማደረግ የሚታገል ድርጅት ነው፡፡ብዙሃኑ ሉኣላዊ ስለጣኑን አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚታገል ድርጅት ነው፡፡ብዙሃኑ በኢትዮጵያ በሚገናባው ፃዕዳ ርእሰማልነት/ነጭ ካፒታሊዝም/capitalism/ፍትሓዊ ተጠቃሚነቱን እንድረጋገጥለት የሚታገል ድርጅት ነው፡፡ሴቶች እኩልነታቸው ተከብሮ በፖለቲካም በኢኮኖሚም ንቁ ተሳታፊዎችና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የሚታገል ድርጅት ነው፡፡ወጣቶች የበይ ተመልካች ሳይሆኑ በኣገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖምያዊ እድገት ዋናው መዘውር በመጨበት ተሳታፊም ተጣቃሚም ለማድረግ የሚታገል ድርጅት ነው፡፡ኢህአደግ ካፒታሊዝም ሲገነባ የስርኣቱ ሞግዚት በሞሆን እንጂ ባለሃብት በሞሆን ኣይደለም፡፡የባለሃብት ስርኣት በሞግዚትነት ለመገንባት ሲታገል ከባለሃብቱ ኪስ ሳይገባ ሞሆን ኣለበት፡፡ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ ኣብዮታዊ ባህሪውን ጠብቆ መሂድ የግድ ይለዋል፡፡

ኢህአዴግ በየመድረኩ መንገራገጭ እየገጠመው ቢመጣም በኣባላቱና በምልኣተ ህዝብ ጠንካራ ትግል ከመንገራገጭ ፈጥኖ እየወጣ ከዛ መንገራገጭ ሲወጣም ፈጣንና መሰረታዊ ለውጥ በሚያመጣ መንገድ እተጠናከረ የሄደ ድርጅት ነው፡፡ኢህአዲግ ከባህሪው የሚመነጭ ችግር ሲገጥመው ጣቱ ወደህዝብ የሚቀስር ሳይሆን ወደራሱ የሚመለከት ድርጅት ነው፡፡በዚህ መልክም ራሱ እያጠራ የመጣ ድርጅት ነው፡፡ኢትዮጵያ በፈጣን እድገት ጎዳና በምትጓዝበት ወቅጥ የታየው ግዝያዊ አለመረጋጋትም ለተፈጠረው ችግር ኢህአዲግ ወደ ውስጡ በማየት ችግሮቹን ለመፍታት ተንቀሳቅሰዋል፡፡ኢህአዲግ ለዚህ ችግር የተዳረገበት ምክንያትም የኢህአዲግ ውስጠ ዲሞክራሲ ኣለመጠናከር፣ስልጣን እንበለ አግባብ መጠቀም ወደ ስልጣን ለመውጣት ሲባል ጥፋታዊ የመተጋገዝ መረብ/network/መዘርጋት እነዚህ ችግሮች ከድርጅቱ ውጭ ወጥተው ወደ ህዝቡም በመድረሳቸው የተፈጠረ ችግር መሆኑን አስቀምጦ ወደ ጥልቅ የመታደስ እንቅስቃሴ ገባ፡፡

በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ህዝቡና ኣባላቱ በቁርጠኝነት መተጋል ካልቻሉ አደጋው ቀላል እንዳማይሆንና የሚከፍሉት ዋጋም መገመት እንዳማይቻል ግንዛበ መፍጠሩ፣ ኢህአዲግ አንዳንድ ኣስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ መጀመሩ የመሳሰሉ ድሎች ቢያስመዘግብም እንደ 1993ቱ ዓ/ም የህዳሴ እንቅስቃሴ ፈጣን ለውጥ ማምጣት ኣልቻለም፡፡ ለምን ?

ባለፉት ግዝያት የተካየዱት ተሃድሶዎች የሚደረግ ትግል የምር፣ ለመድረኩ የሚመጥኑ ኣዳዲስ ኣመለካቶች ከልቡ እየጨበጠ ወደ ግስጋሴው የሚጓዝ የለውጥ ሓይል ስለ ነበነረው ነው፡፡ኣመራር የራሱን ጉድለት ኣፍረጥርጦ በማውጣት ይታገላል፣ ታችኛውም ካላይኛው እየተማረ ይበልጥ ትግሉ ያፋፍመዋል፡፡ድርጅቱ በቁርጠኝነት ለማፅዳት ያለምህረት ጉድለቱን በማየት ለማስወገድ ትግል ያደርጋል፡፡ብዙሃኑም የድርጅቱ ኣመራር ያደረገው

ትግል በመደገፍ፤ መላው አባላቱ ያካየዱትን ሂስና ግለሂስ በማጠናከር፤ ህዝቡ ራሱ ከነበሩት ድክመቶች ለመፅዳት ሰፊ ትግል ያደርጋል፡፡ለህዳሰው ጉዞ ስኬታማነት ከተጠበቀው በላይ ተንቀሳቅሰዋል፡፡

አሁን እየተካሄደ ያለው በጥልቀት የመታደስ ጉዞ ግና እንደ1993ዓ/ም የተካሄደው ተሃድሶ ፈጠን አይደለም፡፡የአሁኑ በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ፈጣን ለውጥ ማምጣት የተሰናው አመራሩ ለነበሩት ጉድለቶች በቁርጠኝነት ለማራጋፍ ዝግጁ ባለመሆኑ የተፈጠረ ነው፡፡አመራሩ ስልጣን በኔትዎርክ መያዝ አለ ስልጣን አለአግባብ መጠቀም አለ ብሎ ስያበቃ ከአመራሩ በዚህ ሂስ የተደረገም የተቀጣም የለም፡፡ክራይ ሰብሳቢነት ውስጣችን ሸብብቦ ይዞናል ተብሎ ሲያበቃ በኮራብሽን ሂስ የተደረጉ ብሎም በህግ የተጠየቁም ሰዎች ከከፍታኛ አመራር በከፊል ብአብዛኛው ከዛ በታች ባሉ ሰዎች የሞሆን አዝማምያ በግልፅ ታየ፡፡የኢህአዲግ ምክርቤት አባላት የኢህአዲግ አባል ድርጅቶች ማእከላይ ኮሚቴዎች በቁርጠኝነት መታገል ያልቻሉበት ምክንያት ቀጥሎ ባለው መንገድ መግለፅ ይቻላል፡፡

ቁጥራቸው የማይናቁ ማእከላይ ኮሚቴ/እንዲሁም ማእከላይ ኮሚቴ የነበሩ/ የሚኖርበት ቤት እንኳን. የሌላቸው እንዳሉ በስፋት ይነገራል፡፡እነዚህ ጓዶች እምቅ አቅም ያለቸውም ናቸው፡፡እያጋጠመ ያለውን ሁኔታ ሲገነዘቡት በተወሰነ ከመፍጨርጨር አልፎው ብዙ ተሰሚነት ያለገኙ ሁነው እናገኛቸዋለን፡፡አልፎአልፎ ተስፋ የመቅረት ሁኔታም ይታይባቸዋል፡፡

በርከት ያለ ቁጥር ያለው ማእከላይ ኮሚቴ አባል ጥቃቅን ጉድለቶች ያሉበት ቢሆንም በድርጅት ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች ደፍሮ እንዳይታገል የክራይ ሰብሳቢው ሓይል ድንፋታ ስለሚያልበት እንዲሁም ፖለቲካል አቅሙ አነስ ስለሚል መውጫ መንገድ በማፈላለግ ላይ የመዳነበር ምልክት የሚታይበት ነው፡፡ይህ ሓይል ከመጀመርያው ከተገለፀው ሓይል በሚገባ ተዋሃህዶ ትግል ካደረገ አሁን እያጋጠመ ያለውን ፈተና ማለፍ የሚችል ሃይል ነው፡፡

ሌላው ክፍል ደግሞ በተለያየ አጋጣሚ ሃብት ያካበተ ወደ ባለሃብትነት የተሸጋገረ ነው፡፡ይህ ክፍል በሁለት መንገድ በመክፈል ማየት ይቻላል፡፡አንደኛው የህዝብ ሃብት እየዘረፈ በሚልዮኖች ብር የሚገመት ሃብት ያካበተ ነው፡፡ይህ ሃይል በምንም ተአምር እጁን የሚሰጥበት ሁኔታ ይፈጠራል ብሎ የሚገመት አይደለም፡፡ትርምሱም የሚፈጥረው ያለው ይህንን ሃይል መሆኑን ጥርጥር የለውም፡፡

ሁለተኛው ክፍል በተለያየ አጋጠሚ ሃብት ያከበተ ክፍል ሞኖሩ ነው፡፡ይህንን ክፍል ከወላጆቹ ወይም ከወዳጆቹ በውርስ ያገኘው ሃብት ሊሆን ይችላል፡፡ሌላው ደግሞ የከመንግስት በሚያገኘው ደመወዝ ጥቅማጥቅም ተጠቀምሞም ሃብት ያካበተ ሊኖር ይችላል፡፡ይህ ሃይል ያካበተው ሃብት “ማንኛውም ሃብታም በስተጀርባው አንዳች ወንጀል አለው” የሚል የሸክስፒር አባባል እያስተወሰ አንተስ ከየት አመጣሃው ተብሎ እንዳይጠየቅ በመስጋት ከመታገል ዝምታን የመረጠ ነው፡፡በርግጥ ሃብት መኖር ለመዋለዋል እድል የሚሰጥ በሞሆኑ እነዚህ ወገኖች መወላወላቸው የሚገርም አይደለም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ስላሉ ነው እንዳይነካካ ፈርቶ እኛ ማስረጃ የለንም፣ማስረጃ ካላቹህ ንገሩን እርምጃ እንወስዳለን ወደሚል የተሸጋገረው፡፡አባላቱና ህዝቡም በቅርበት የሚታወቁ ማስረጃ ካጡ ማን እንዲነግራቸው ፈለጉ ወዲሚል ተሸጋገረ፡፡ያለውን ችግር በቅጡ ሳይፈታ ኢህአዲግ አከታትሎ በርከት ያሉ ዶክቶሮች መሾም ጀመረ፡፡ይህም ሌላ ጥያቄ ቀሰቀሰ መሪ ማነው? ማንኛውም የተማረው? ወይስ መድረክ የፈጠረው? በነዚህ በጥልቀት የመታደስ ጉዞ እንዳለፈው የ1993ዓ/ም የህዳሴ እንቅስቃሴ እምርታን መፍጠር ተሳነው፡፡

ውድ አንባብያን ችግሮቹ እነዚህ ከሆኑ መፍትሄዎቹስ ምንድናቸው?ብለው መጠያቃቸው አይቀርም፡፡መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትን ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

ዋነኛ መፍትሄ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨብጦታል፡፡መሪ ድርጅት ያስፈልገው ነበር የህዝብ ብሶት የወለደው ድርጅት ኢህአዴግ አለው፡፡የጠራ መስመር ያስፍለገው ነበር በየግዜው እየጠራና እየተጠናከረ የመጣ የጠራ መስመር አለው፡፡ለዚህ ኣላማ ተፈፃሚነትም የሚዋደቁለት ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆችም አሉት፡፡ምልኣተ ህዝብ የተጀመረውን የህዳሴ እንቅስቃሴ በማጠናከር እየተመዘገቡ ያሉትን የልማትና የዲሞክራሲ እድገቶች እንዲቀጥሉ ይፈልጋል፡፡ለማስቀጠልም ማንኛውም መስዋእትነት ለመክፈል ዝጉጁ ነው፡፡ ከዚህ በታች የሚቀርቡት መፍትሄዎች ይህንን ከላይ የተገለፁትን ግንዛቤ በማስገባት ነው፡፡

## 1.ኢህአዲግ ራሱን የማጥራት ጉዳይ ከከፍተኛ ኣመራር መጀመር ኣለበት፡፡

መሪዎች ለተከታዮቻቸው ተምስሌት መሆን ይገባቸዋል፡፡ታላቁ መሪ መለስ የዓሳ ግማቱ ከጭቅላቱ የሚል ኣባባል ይጠቀም እንደበረ ይነገራል፡፡እውነት ነው፡፡ታላቁ መሪ መለስ ችግሮች ሲከሰቱ ወደ ውጭ ሳይሆን ወደ ውስጥ በመመልከት መፍትሄ እንደሚገኝ ፅኑ እምነት የነበረው መሪ ነው፡፡መለስ በሂወት በነበረበት ወቅት የተካሄዱት ተሃድሶዎች ውጤታማ የሆኑበት ምክንያት በህዳሴው ወቅት የሚወሰኑ ውሳኔዎች ከልቡ ተቀብሎ ለተግባረዊነታቸው ይራበርብ ስለ ነበር ነው፡፡ኣሁን ያለውን ኣመራር የመለስን ፈልግ ተክትሎ መተግበር ይጠበቅበታል፡፡

ኣመራሩ ከማጥራት ተያይዞ ያለውን ጉዳይ ለየት ባለ መንገድም መታየት ኣለበት፡፡ በማንኛውም መንገድ ሃብት በማካበት ወደ ባለሃብትነት የተሸጋገሩ ኣመራሮች እስከኣሁን ድረስ ላበረከቱት ኣስተዋፅኦ በማመስገን ከሃላፍነታቸው ማሰናበት ይገባል፡፡ይህንን ተግባር ያለምንም ማቅማማት መተግበር ኣለበት፡፡ኢህኣዲግ ማንኛውም ባለሃብት ከደጋፍነት ኣልፎ በኣባልነት ደረጃ እንኳን ኣይመለምልም፡፡ባለሃብት በኣባልነት ደረጃ የማይመልምለበት ምክንያት ኢህኣዲግ ህብረተሰባዊ መሰረቱ ባለሃብት ስላልሆነ ነው፡፡ስለዚህ ኣመራሮቹ በተገኘው ኣጋጣሚ ወደ ባለሃብተነት ሲሸጋገሩ ከአመራራቸው ማሰናበት ይገባል፡፡ከዚህ በመቀጠል መሰራት ያለበት ወደ ባለሃብትነት ተሻጋግራቹሃል ተብለው የተሰናበቱትን የሃብታቸውን ምንጭ መምርመር ኣለበት፡፡በክራይ ሰብሳቢ መንገድ የተገኘ ከሆነ ወደህግ የሚቀርቡበት ሁኔታ መፈጠር ኣለበት፡፡በውርስና የተላየየ ንፁህ

የሃብት ማካበት ከሆነ ደግሞ ነፃ ሁኖው እንደማንኛውም ዜጋ ሃብታቸውን የሚያስተደድሩበትና ከሃብታቸው የሚጠቅመበት መንገድ ተከትለው ይኖራሉ፡፡

**2.በኣመራር የተሎኮሰውን የትግል ችቦ ይዞ ወደ ኣባላቱ በመቅረብ ሰፊ ትግል ማካየድ፡፡**

የድርጅቱ ኣባላት ራሱን ያጠራ ኣመራር ሲመራው ወደ ጋለ ትግል ገብቶ ኣስፈላግውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ የመሆን እድል ስለሚፈጠር ትግሉ እስካሁን እንደነበረ ሁኔታ የተወሳሰበ ኣይሆንም፡፡በድርጅት ኣባላት የሚካየድውን የማጥራት ስራ ፍፁም ዲሞክራስያዊ ከመጠቃቃት የጠራ በሆነ መንገድ መምራትን ይጠይቃል፡፡በዚህ ኣይነት ዲሞክራስያዊ መንገድ የማጥራት ስራ ያከናወነ ኣባል ወደ ህዝቡ በመግባት ትግሉን ማቃጠጠል ይኖርበታል፡፡

**3.በዚህ የህዳሴ ጉዞ ብዙሃኑ ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ መምራት**

ብዙሃኑ እየጠበቀው ያለ ኢህኣዲግ ወደ ገዢ መደብ ሊያሸጋግረው የሚችል ኣደጋ ተወግዶ ኣብዮታዊ ዲሞክራስያዊ ባህሪውን ጠብቆ ብዙሃኑ የሚጠቀሙበት ካፒታሊዝም ስርኣት ግንባታው እንዲጠናከር ነው፡፡ራሱን ያጠራ ድርጅት ብዙሃኑ ለጋለ ትግል መቀስቀስ ማተገል ይጠበቅባታል፡፡

ብዙሃኑ ህዝብም ኢህኣዲግ ወደ ገዢ መደብ ሳይሸጋገር ኣብዮታዊ ዲሞክራስያዊ ባህሪው ጠብቆ እንዲቆይ ወሳኝ ትግሉ ማካየድ ኣለበት፡፡ምንኣገባኝ ድርጅቱ ራሱ ያውቀውየለ የሚሉ ሃላቀር ኣስተሳቦች ማስወገድ ይጠበቃል፡፡

**4. ኢህኣደግ መድረክ የፈጠረውን መሪ ማሰባሰብ ማደራጀትና አቅሙን መገንባት ኣለበት**

በቅርብ ግዜ ስልጣን የተሰጣቸው ዶክቶሮች/ሙሁራኖች/ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ የህዝብን ችግር ሲፈቱ እያየቸው የመጡ ኣይደሉም፡፡መድረክ የፈጠራቸው ለሞሆናቸው ህዝቡ ይቅርና የድርጅቱ ኣባላትም እርገጠኛ ኣይደሉም፡፡ይህንን ችግር መወገድ ኣለበት፡፡

መሪ የተማረ/ኣዋቂ/ መሆን እንዳለበት ምንም ጥርጥር የለውም፡፡መላው ማህበረሰብም ካልተማረ በስራ ካልሰለጠነ ጠንካራ ሃገር መፍጠር ኣይችልም፡፡ኢትዮጵያ ኣሁን የደረስችበት ሁኔታ እንኳን በከፍተኛ ኣመራር ይቅር በቀበሌ የሚኖር ኣመራር የተማረ ሞሆን እንዳለበት በግልፅ እየታየ ነው፡፡ጥያቄው ግን ማንኛውንን የተማረ ነውወይ መሪ የሚሆነው ወይስ መድረኩ የፈጠረው ነው ጥያቄው፡፡ማንኛውም የተማረ መሪ መሆን ኣይችልም፡፡መሪ በማህበረሰብ ውስጥ በሚካየድ የጋለ ትግል ነው የሚወለደውና የሚያድገው፡፡በየደረጃው የሚመደብ ወይም የሚመረጥ መድረክ የፈጠረው መሆን ኣለበት፡፡የኢትዮጵያ ህዝቦች ኣብዮታዊ ዲሞክራሲ ግንባር መስመር በውል የተገነዘበ እስከ መስዋእትነት ዝግጁ የሆነ ታግሎ የሚያታግል ህዝቡ እያገጠሙት ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የህዝብ ኣገልጋይነት ባለው መንፈስ የሚመራመር መፍትሂ የሚያስቀምጥ ያስቀመጠው መፍትሂም በህዝቡ ተጣቃሚነት ኣይን ኣይቶ ለተግባራዊነት የሚረባረብ መሆን ኣለበት፡፡

**5.የኢህአዲግ ኣባል ድርጅቶች ወደ ማእከላይ ኮሚቴ የሚያመጡትን ሰው በባለሃብትነት የማይታይ መሆን እንዳለበት በውስጠ ድርጅታቸው ሕገ-ደምብ በግልፅ ማስቀመጥ ኣለባቸው፡፡**

ኢህአዲግ ልማታዊ ባለሃብቶች እንዲፈጠሩ የሚመራ ድርጅት እንጂ የባለሃብቶች ድርጅት ኣይደለም፡፡ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ ባለሃብቶች የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅላቸው ድርጅት መፍጠር እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ኢህኣዴግ ግን የኣርሶኣደሮች ሰራተኞች፣በዝቅተኛ ኑሮ የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች እንዲሁም የኣብዮታዊ ሙሁራን ድርጅት ነው፡፡ወደ ማእከላይ ኮሚቴነት መመረጥ ካለባቸውም ከነዚህ ማሕበራሰባዊ ክፍል ብቻ መሆን ኣለበት፡፡ይህንን ማድረግ ካልቻለ ያለምንም ጥርጥር ኢህአዴግ ወደ ገዢ መደብ የሚሸጋገርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ይህንን ኣደጋ ለማስወገድ በባለሃብት የሚታይን ሰው ወዳማእከላይ ኮሚቴ እንዳይመረጥ የሚከለክል የውስጥ ድርጅት ህገ-ደምብ በግልፅ መስፍር ኣለበት፡፡

ሌላ ትኩረት መሰጠት ያለበት ኢህኣዴግ የሚመራው መንግስት ውስጥ የደመወዝ የኣበል እንዲሁም የተላያዩ ጥቅማጥቅሞች ኣወሳሰን ላይም ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል፡፡የደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥሞች ኣወሳሰን በተመለከተ ወደስልጣን/ሓላፊነት/የሚወጣውን ሰው ወደገዢ መደብ/ባለሃብትነት/ሊያሸጋግረው በሚያስችል ሁኔታ መወሰን የለበትም፡፡የህዝብ ኣገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ለኑሮው የሚበቃው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ብቻ ማግኘት ኣለበት፡፡

ይህ ሲሆን ነው ወደስልጣን ሲወጣ የሚያገኘው ጥቅም ኣማልሎት ሳይሆን ህዝብን ለማገልገል የቆረጠ መሪ ማምጣት የሚቻለው፡፡


ታጁ ሙሓመድያሲን

Email-tajumuhamedyassin@gmail.com